የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDRAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ—ሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 28
ADDIS ABABA–2nd July, 2002


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፩/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
የቴሌኮሙኒኬሽን (ማሻሻያ)
አዋጅ ........................................................ ፩ሺ፯፻፹


## CONTENTS


Proclamation No. 281/2002
Telecommunications (Amendment)
Proclamation ........................................ page 1780


### አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፩/፲፱፻፺፬
### የቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅን ለማሻሻል
### የወጣ አዋጅ

በቴሌኮሙኒኬሽን መስክ በአፈጻጸም ችግር ያስከተሉ አሠራሮችን ማሻሻል እና አዳዲስ አሠራሮችን ማስተዋወቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በቴክኖሎጂና በዓለም አቀፍ የአሠራር ለውጦች ምክንያት የተፈጠሩ አዳዲስ ሬጉላቶሪ ሁኔታዎችን በሕጋችን ውስጥ ማካተት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የቴሌኮሙኒኬሽን (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፩/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ማሻሻያ</u>

የቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር ፵፱/፲፱፻፹፱ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል፤

"፫· "ብቸኛ የሆነው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት" ማለት በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲/፲፱፻፹፱ የተቋቋመው ኮርፖሬሽን ወይም ኮርፖሬሽኑን ተክቶ የሚቋቋም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ነው፣

### *PROCLAMATION NO. 281/2002*
### *A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF TELECOMMUNICATIONS PROCLAMATION*

WHEREAS, it has become imperative to properly address difficulties encountered in the implementation process in the telecommunication sub-sector and introduce new working methods for same;

WHEREAS, it has become imperative to incorporate new regulatory conditions resulting from technological and operational changes at the international level;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Telecommunications (Amendment) Proclamation No. 281/2002."

2. *Amendment*

   Telecommunications Proclamation No. 49/1996 is hereby amended as follows:

   1) The following new Sub-Articles (3) and (4) are added under Article 2 of the Proclamation:

      "3) "Sole Telecommunications Service Provider" means the Corporation established by the Ethiopian Telecommunications Corporation Establishment Council of Ministers Regulations No. 10/1996 or any service provider that replaces it."

፬. "የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት" ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን ማዞሪያዎች አገልግሎት ሴሉላር ሞባይል አገልግሎት ፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ፣ የሳተላይት ቴሌፎን አገልግሎት ፣ የዳታ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፣ የቴሌ ሴንተር ወይም ሪሴል አገልግሎት ፣ የተንቀሳቃሽ ወይም የቋሚ የግል ሬዲዮ አገልግሎት ፣ የቪሳት አገልግሎት ፣ የኬብል መዘርጋትና ጥገና ሥራ ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ማዞሪያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራ ፣ በኤሌክትሪክ ወይም በኤሌክትሮ ማግኔቲክ ኃይል አማካይነት በስልክ ሽቦ ፣ በሬዲዮ ፣ በኦፕቲካል ፋይበር ወይም በሌላ ኤሌክትሮ ማግኔቲክ ወይም ማናቸውም ሌላ ሥልት ድምፅ ፣ ምልክት ፣ ፅሁፍ ወይም ምስል ማሰራጨት ወይም መቀበል ፣ እንዲሁም ሚኒስቴሩ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ብሎ የሚወስናቸውንም የሚጨምር ሲሆን የብሮድካስቲንግ አገልግሎት እና የኢንተርኮም ግንኙነትን አይጨምርም።"

፪. የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፮) ተተክቷል ፣

"፮. "የኮልባክ አገልግሎት" ማለት የሀገር ውስጥ የቴሌኮሙኒኬሽን ድርጅት ሳያውቀው የሌላ ሀገር የቴሌኮሙኒኬሽን ድርጅት የጥሪ ቶንን ለኢንተርናሽናል ግንኙነት መጠቀም ሲሆን በዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ሕብረት ኮልባክ ተብለው የሚታወቁ አገልግሎቶችን ይጨምራል።"

፫. የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፫)፣ (፬)፣ (፭)፣ (፮)፣ (፯)፣ እና (፰) እንደ ቅደም ተከተላቸው (፭)፣ (፮)፣ (፯)፣ (፰)፣ (፱)፣ እና (፲) ሆነዋል ።

፬. በአዋጁ አንቀፅ ፮ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፰) እና (፱) ተጨምረዋል ፤

"፰. ለሳተላይት ቴሌፎን ድርጅቶች በቅድሚያ ብቸኛ ከሆነው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ጋር በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት ሲግናሎች ለመላክና ከኢትዮጵያ የሚላኩትንም ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል ፣

፱. በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም ችግሮች ሲከሰቱና ሚኒስቴሩም ይህን በተመለከተ መመሪያ ሲያወጣ ኤጀንሲው ብቸኛ የሆነው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት አስፈላጊውን የአደጋ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት እንዲሰጥ ወይም ከሌሎች ጋር በመስማማት እንዲያቀርብ ያደርጋል ፣ ለዚህም በግልፅ ከተወሰኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ሬጉላቶሪ ሁኔታዎች ነፃ የመሆን መብት ይሰጣል።"

፭. የአዋጁ አንቀፅ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፰)፣ (፱)፣ (፲)፣ (፲፩) እና (፲፪) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀፅ (፲)፣ (፲፩)፣ (፲፪)፣(፲፫) እና (፲፬) ሆነዋል ።

፮. በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፫)(ለ) ውስጥ "መንግሥት" የሚለው ቃል "ሚኒስቴሩ" በሚለው ቃል ተተክቷል ።

፯. በአዋጁ አንቀጽ ፲ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል ፣

4) "Telecommunication Service" means Public Switched Telecommunication Service; Cellular Mobile Service; Interned Service; Satellite Telephone Service; Data Communication Service; Telecenters or Resale Service; Mobile or Fixed Private Radio Service; VSAT (Very Small Aperture Terminal) Service; Cable Installation and Maintenance Service; Telecommunication Switches Installation and Maintenance Service; the transmission or reception through the agency of electricity or electromagnetism of any sounds, signs, signals, writing, images or intelligence of any nature by wire, radio, optical fiber, or other electromagnetic system or any other service designated as Telecommunication Service by the Ministry. It shall not include Broadcasting Service and Intercom Connections."

2) Sub-Article (6) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (6):

"6) "Call-back Service" means the use of dial tone of a foreign telecommunication operator for international connections without the knowledge of the domestic telecommunication operator and shall include services that are identified as call-back by the International Telecommunication Union."

3) Sub-Articles (3), (4), (5), (6), (7) and (8) of Article 2 of the Proclamation are re-numbered as Sub-Articles (5), (6), (7), (8), (9), and (10), respectively.

4) The following new Sub-Articles (8) and (9) are added under Article 6 of the Proclamation:

"8) to issue license to satellite companies so as to allow them to send and receive signals to and from Ethiopia, provided that such companies shall first enter into agreement with the Sole Telecommunication Service Provider;

9) to compel the Sole Telcommunication Service Provider to provide the necessary disaster communication service by itself or by entering into agreement with others, where a natural disaster or problem occurs in Ethiopia and the Ministry issues a directive to this effect. The Agency, in such cases, shall exempt the Sole Telecommunication Service Provider from specifically stipulated regulatory conditions."

5) Sub-Articles (8), (9), (10), (11) and (12) of Article 6 of the Proclamation are re-numbered as Sub-Articles (10), (11), (12), (13), and (14), respectively.

6) The word "Government" under Sub-Article (3) (b) of Article 7 shall be replaced by the word "Ministry"

7) The following new Sub-Articles (3) and (4) are added under Article 10 of the Proclamation:

"፫· በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ አንቀፅ ፭(፪)(ለ) የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ፣ ኤጀንሲው ፣
 ሀ) በቴሌ ሴንተር ወይም ሪሴል አገልግሎት ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ፣
 ለ) የውጭ ኬብል ወይም ከማዞሪያ እስከ ደንበኛ ቤት የሚዘረጉ ገመድ አልባ መስመሮችን የመትከል ወይም የመጠገን ሥራ ላይ ለሚሰማሩ፤
 ሐ) የቴሌኮሙኒኬሽን ማዞሪያዎችን የመትከል ወይም የመጠገን ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ፣
 መ) በአንድ ሕንፃ ወይም ቤት ውስጥ መስመር የመዘርጋት ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ፤ ወይም
 ሠ) ሌሎች ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይ በሆኑና ሚኒስቴሩ በመመሪያ በሚወስናቸው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ላይ ለሚሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል ።
፬· በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፫) መሠረት ኤጀንሲው ፈቃዱን ለመስጠት የሚያስችለው መመሪያዎች ሚኒስቴሩ ማውጣት አለበት ።"

፰· በአዋጁ አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ (፫) ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (ለ) ተጨምሯል ፣

"ለ) መሣሪያው ለንግድ የሚውል ከሆነ አስመጪው ላስመጣው መሣሪያ መለዋወጫ ለማቅረብና ለመጠገን ያለው የመሣሪያ ፣ የገንዘብና የሰው ኃይል አቅም፤።"

፱· የአዋጁ አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ ፫ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ) እና (ረ) እንደቅደም ተከተላቸው (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ) እና (ሰ) ሆነዋል ።

፲· የአዋጁ አንቀፅ ፳፬ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተተክቷል ፣

"፪· ኮልባክ አገልግሎት መጠቀም ወይም የኮልባክ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው።"

፲፩· በአዋጁ አንቀፅ ፳፬ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል ፣

"፫· ኢንተርኔትን በመጠቀም የድምፅ ወይም የፋክስ መልዕክትን ማስተላለፍ ወይም የማስተላለፍ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው ።

፬·ማንኛውም ሰው ፈቃድ ካልኖረው በስተቀር የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ የዘረጋውን ኔትወርክ ተጠቅሞም ሆነ ሳይጠቀም ለግልም ይሁን ለንግድ የቴሌኮሙኒኬሽን ሥራ መስራት አይችልም።"

፲፪· በአዋጁ አንቀፅ ፳፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) ውስጥ "የዚህን አዋጅ አንቀፅ ፲፭(፪) ወይም ፳፬(፪)" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "፳፬(፫) ወይም ፳፬(፬)" የሚል አዲስ ሀረግ ተጨምሯል ፣

፲፫· በአዋጁ አንቀፅ ፳፭ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተጨምሯል ፤

"፩·በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የፀና ፈቃድ ሳይኖረው አገልግሎት የሰጠ ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ በሰራበት ጊዜ ውስጥ ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚወሰነውን ገቢ እጥፍ የገንዘብ መቀጮና ከ፫ እስከ ፭ ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።"

፲፬· የአዋጁ አንቀፅ ፳፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) ፣ (፪) እና (፫) እንደቅደም ተከተላቸው ፣ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፣ (፫) እና (፬) ሆነዋል።

፫· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



"3) Notwithstanding the provision of Article 5(2) (b) of Proclamation No. 280/2002, the Agency shall issue license to individuals or companies participating in the following services:
 (a) Telecenters or resale service;
 (b) Outside cabling or Wireless Local Loop lines installation or maintenance;
 (c) Telecommunication exchange installation or maintenance;
 (d) In-house or building cable installation;
 (e) Other similar activities to be designated by the directives of the Ministry.
4) The Ministry shall issue directives so as to enable the Agency to issue the license specified under Sub-Article (3) of this Article."

8) The following new Sub-Article (b) is added under Sub-Article (3) of Article 14 of the Proclamation:

"(b) if the equipment is imported for profit, the importer's material, financial and human resource capability to supply spare parts and provide maintenance service for the equipment imported;"

9) Sub-Articles (3) (b), (c), (d), (e) and (f) of Article 14 of the Proclamation are re-numbered as (3) (c), (d), (e), (f), and (g) respectively.

10) Sub-Article (2) of Article 24 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2):

"2) The use or provision of call-back service is prohibited."

11) The following new Sub-Articles (3) and (4) are added under Article 24 of the Proclamation.

"3) The use or provision of voice communication or fax services through the internet are prohibited;

4) No person shall, using the telecommunication service provider network, or bypassing same, engage in private or Commercial Telecommunication Services unless a license is issued to it."

12) Under Sub-Article (1) of Article 25, a new phrase "24(3) or 24(4)" is added next to the phrase "the provisions of Article 15(2) or 24(2)".

13) The following new Sub-Article (1) is added under Article 25 of the Proclamation:

"1) Any person who engages in telecommunication services without having a license or a valid license as per this Proclamation or any other relevant laws shall be punished with fine equal to double the revenue estimated to have been earned by the person during the period of time he operated the service and with imprisonment from 3 upto 5 years".

14) Sub Articles (1), (2) and (3) of Article 25 of the proclamation are re-numbered as sub-Articles (2),(3) and (4) respectively.

3. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 2nd day of July, 2002.

Done at Addis Ababa, on the 2nd day of July, 2002.

*GIRMA WOLDE GIORGIS*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL*
*DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
*BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE*